# በኢትዮጵያ የአወራረስ ሕግ ውስጥ የተካተተው የምርጫ መሠረተ ሀሳብና የገንዘብ ጠያቂዎች መብት

በጥላሁን ተሾመ*

በመሞቱ ላይ ብድር ቢኖርበት ይስጡ፥ መሞቱ የተወው ገንዘብ ብድሩን ለመክፈል የማይበቃ ቢሆን ልጆች ካልወረሱ ዕዳውን ብድሩን ለመክፈል አይገባውም። የወረሰ ቢሆን ግን ለይቶ ቁጥሩን ጽፎ ያኑር፥ ለባለዕዳች ቁጥሩን ይንገሩቸው ፥ ለያንዳንዱ እንደገንዘቡ መብዛትና ማነስ ይሰጣቸው፥ ተተብሎ የወንድ ልጅ ግጣ የሴት ትልወት አድርጎ ቢሰጣት ፥ ወረታ አድርጎ ቢመጣት ፥ መውር ቢያስቀር ፥ ከገንዘባቸው ባዶቸውን ቢሰጣቸው ወደ ባይነግሩቸው ፥ እኩሌታውን መተቶ እኩሌታውን ቢነሳቸው መሳውን ሊከፍላቸው ይገባል። ጅራቷ ታድርሰኝ ከእናቷ እንጊሉ ፥ ነገሩ አፋቸውለቀርባን እንገታቸውለማተብ በበቀደጋገ ሰዎች ከታወቀ በኋላ ሊከፍላቸው ይገባል።[1]

## I

አንድ ሰው ሀብት አፍርቶ ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ ተራፊ ንብረቱ እንደተለየ ሀብት ተቆጥሮ ሕጉ የውርስ አጣሪ ብሎ በሚለይማቸው ሰዎች አስተዳደር ሥር ይቆያል። የዚህ ዓይነት ሥራ የሚያካሂዱት ውርስ አጣሪዎች ተግባሩን ለማከናወን የሚያስችላቸውን ሥልጣን በልዩ ልዩ መንገዶች ሊያገኙ ይችላሉ። ሟቹ በኑዛዜው ላይ ይህን ሥራ እንዲሠሩ በኑዛዜ አስፈጻሚነት ሊለይማቸው ይችላል። ሟቹ ኑዛዜ ያልተወ እንደሆነ ወይም ኑዛዜ ትቶም ቢሆን በኑዛዜው ላይ የኑዛዜ አስፈጻሚ አልሰየመ እንደሆነ ሕግ ለይቶ የሚያመለክታቸው ሰዎች የውርስ አጣሪነቱን ሥራ ለማካሄድ መብት ይኖራቸዋል። ያለኑዛዜ ለሟቹ ወራሽ ለመሆን የሚችሉ ሰዎችና ሟቹ በኑዛዜው ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ተቀባይ ያደረጋቸው ሰዎች ያለአንዳች ፎርማሊቲ የውርስ አጣሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሕጉ ይናገራል። የሟቹ ወራሾች እነማን እንደሆኑ ያልታወቀ እንደሆነ፥ ወይም ወራሾቹ ውርሱን እንፈልግም ያሉ እንደሆነ፥ ወይም የውርስ ማጣራቱን ሥራ ለመሥራት ያልፈቀዱ እንደሆነ፥ ሟች ወራሾች የሌሉት ሆኖ መንግሥት የውርስ ተቀባይ እንዲሆን የተጠራ እንደሆነ፥ ዳኞች የውርስ አጣሪ የሚሆነውን ሰው ይሰይማሉ። ከዚህም ሌላ ሟቹ በኑዛዜው ላይ የኑዛዜ አስፈጻሚ ቢሾምም የኑዛዜው ውጤታማ መሆን አጠራጣሪ ከሆነ ወይም የውርስ አጣሪ ሆነው ንብረቱን የማስተዳደሩን ተግባር ለማከናወን መብት ባላቸው ሰዎች መሀል ሥራውን በተመለከተ ስምምነት የታጣ እንደሆነ፥ አለበለዚያም የሟች ወራሽ የሆነው ሰው በልዩ ልዩ ምክንያቶች የራሱን መብት መጠበቅ የማይችል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፥ ዳኞች ሌላ ገለልተኛ የሆነ የውርስ አጣሪ መሰየም ይችላሉ።[2]

---

* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ረዳት ፕሮፌሰር ፥ ቀደም ሲል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩ።

1 ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው፥ በ1958 ዓ.ም አዲስ አበባ በብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፥ 42ኛ አንቀጽ ፥ በእንተ ርስት ፥ ገጽ 458 እና 459፥

2 የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 946 እስከ 951 ይመልከቱ። ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952 ዓ.ም በተለይ የወጣ፥ አዋጅ ቁጥር 165/1952 ዓ.ም፥

በኢትዮጵያ የአወራረስ ሕግ ውስጥ የተካተተው የውርስ ማጣራት ሂደት[3] ውርስ አጣሪው የሟቹን የቀብር ሥነ ሥርዓትና የመታሰቢያ ዝክረ ነገሮች ከማስፈጸም ጀምሮ፣ የውርሱን ተጠቃሚዎች ማንነት መወሰንን፣ የውርሱ አካል የሆኑትን ልዩ ልዩ ንብረቶች መሰብሰብንና እንዲጠበቁ ማድረግን፣ የውርሱን ንብረት ዝርዝር ማዘጋጀትንና የገምቱን ስሌት ማውጣትን፣ የተረጋገጡና የመክፈያ ጊዜያቸው የደረሱ የውርሱን ዕዳዎች መክፈልን፣ ለልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚዎች በሟቹ የተደረጉ ስጦታዎችን ማስረከብንና፣ ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን መፈጸምን አስመልክቶ የሚያከናውናቸውን ተግባሮች ሁሉ የሚጨምር ሥራ ነው።

የዚህ ፅሁፍ ትኩረት ግን ከዚህ ሰፊ ክንዋኔ ውስጥ እንዱን ክፍል ብቻ የሚዳስስና የውርስ ተጠቃሚ በሚሆኑ ሰዎች እና ከውርሱ ላይ የገንዘብ ጥያቄ በሚያቀርቡት ባለመብቶች መሀከል ያለውን ግንኙነት የሚፈትሽ ነው።

## II

በውርስ ሀብት ላይ አብዛኛውን ጊዜ የይገባናል ጥያቄ የሚያነሱት አንድም በኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች አለበለዝያም የውርሱ ገንዘብ ጠያቂዎች እየተባሉ የሚጠሩት የሟቹ ሰው ባለገንዘቦች ናቸው።[4]

ወራሾችንና ሌሎች የኑዛዜ ተጠቃሚዎችን በተመለከተ ውርሱን የመቀበልና ያለመቀበል ምርጫ ያላቸው መሆኑን ሕጉ ያመለክታል። ከአወራረስ ሕግ ጋር በተያያዘ ምርጫ የሚለው አነጋገር በኑዛዜ ወይም ያለ ኑዛዜ የውርስ ተጠቃሚ የመሆን መብት ያላቸው ሰዎች የውርሱን ጥቅም ለመቀበል ወይም ላለመቀበል በግል የሚሠጡትን ውሳኔ የሚያመለክት ነው። ወደኋላ እንደምንመለከተው ይህን ውሳኔ መስጠት አልፎ አልፎ አዳጋች የሚሆንበት አጋጣሚም አይታጣም። በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ሕግ ውስጥ እንዲካተት የተደረገውና "<u>የአስፈላጊዎች ወራሾች አለመኖር</u>" የሚለው ደንብ "ማናቸውም ወራሽ እንዲወርስ የተጠራበትን ውርስ ወይም የኑዛዜ ስጦታ ለመቀበል አይገደድም" በማለት የሚደነግግ ነው።[5] ይህ በሲቪልም ሆነ በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓቶች የሚሠራበት ደንብ "አንድ ሰው እንድን ተለይቶ የሚታወቅ ጉዳይ አስመልክቶ የሁለት እርስ በርሳቸው ሊጣጣሙ የማይችሉ መብቶች ባለቤት እንዲሆን ሊፈቀድለት

---

[3] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 5፣ ምዕራፍ 2፣ ቁጥር 942 እስከ 1059፣

[4] የሞተ ሰው የመብት ተጠቃሚም ሆነ የግዴታ ተጠያቂ ሊሆን ስለማይችል ነው፣ ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 1፣

[5] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 976፣ እንደዚሁም "ማንም ሰው የተጠራበትን ውርስ እንዲቀበል አይገደድም" የሚለውን የፈረንሣይ የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 775 ይመልከቱ ፣ ትርጉም የጸሐፊው ሲሆን ጥቅሱ የተወሰደው <u>ማርሴል ፕላንዮል "የፍትሐ ብሄር ሕ</u> <u>!የመጀመርያ ደረጃ ሐተታ"</u>በማለት ከጻፉትና በሉዊዝያና ግዛት የሕግ ተቋም ከፈረንሣይኛ ወደእንግሊዝኛ ከተተረጎመው መጽሐፍ 3ኛ ሽልዩም ፣ክፍል 1፣ እ.ኤ.አ. 1959 የታተመ ፣ ገጽ 616 ነው።

አይገባም በሚለው ሚዛናዊ መሠረት ላይ የቆመ ነው።"[6] በመሆኑም የሟቹን ትሩፋት የተቀበለው ወራሽ ወይም የኑዛዜ ተጠቃሚ ይህ ያገኘው ትሩፋት የሚያስከትልበትን ግዴታ ለመወጣት የተዘጋጀ እንዲሆን ይገባል። ማንም ሰው ቢሆን ጥቅም የሚቀበለው ጥቅሙ የሚያስከትለውን መጠነኛ እንግልትም አብሮ በመቀበል ነውና።

ውርሱንየመቀበልና ያለመቀበል ምርጫ የወራሹ ወይም የኑዛዜ ተጠቃሚውና የእርሱ ብቻ የሆነ መብት ነው። ተጠቃሚው በህይወት እስካለ ድረስ ማንም ሰው በምንም ዓይነት ሁኔታ በእሱ ምትክ ሆኖ ውርሱን እፈልጋለሁ ወይም አልፈልግም ብሎ ለመምረጥ አይቻለውም።[7] ከወራሹ ላይ በግል ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎችም ቢሆኑ ውርሱንእንዲቀበል የማስገደድ መብት የላቸውም። ይሁንና ውርሱንአልፈልግም ያለው በእኛ ላይ ጉዳት ለማድረስ ነው የሚል መቃወምያ እነዚህ ባለገንዘቦች አንስተው እንዲከራከሩ ሕግ ይፈቅድላቸዋል።[8]

ወራሹ የምርጫ መብቱን የሚሠራበት ውርሱንየሚቀበል ወይም የማይቀበል መሆኑን ቁርጠኛ በሆነ ቃል በማረጋገጥ ነው። በውርስአመራረጥ መርህ መሠረት ወራሹ ውርሱንከተቀበለ ሙሉ በሙሉ ተቀብሏል፣ አልፈልግም ካለም መብቱን ሙሉ በሙሉ ትቶታል ማለት ነው።[9] ወራሹ ውርሱንለአንድ ጉዳይ ተቀብያለሁ ካለ ለሁሉም ጉዳይ እንደተቀበለና መቀበሉ በሚያስከትለው ውጤት ሁሉ ለመስማማት ፈቃደኛ መሆኑን እንደገለጸ ሕግ ግምት ይወስዳል።[10]

በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ሕግ ለየት ያለ አካሄድን ለመከተል የመረጠ ቢመስልም የምርጫ መብትን አስመልክተው የሲቪልም ሆነ የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓቶች ዝርዝር አሠራሩን እንደሚከተለው ያስቀምጡታል።

---

6 <u>ክርፐስ ጁሪስ ሰኮንዶም</u> በመባል ከሚታወቀው መላው የአሜሪካ ግዛት ሕጎች ከተተነተኑበት ባለበርካታ ቅጽ መጽሐፍ ውስጥ፣ ስለኑዛዜ ከሚናገረው ከ97ኛው ቮልዩም የተወሰደ፣ አንቀጽ 1237፣ ገጽ 8፣ ትርጉም የራሴ፣

7 የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 977 (1)፣ 853፣

8 ዝኒ ከማሁ ፣ ቁጥር 993 ፣ ከቁጥር 9772 (2) እና (3) ጋር ያገናዝቧል ፣ በዚህ አንቀጽ የሠፈረው ደንብ የአንድ ወራሽ ባለገንዘብ የሆኑ ሰዎች ይህ ወራሽ የእነሱን መብት ሊጎዳ በሚችል ተንኮል ጠቀስ ተግባር ውርሱንለቅቄያለሁ በሚልበት ጊዜ የመቃወም መብት የሚያገኙበት አሠራር ነው። ይህን ፍሬ ሀሳበ በተመለከተ እምስና ዋልተን የተባሉ ጸሀፍት ፣ "<u>የፈረንሣይ ሕግ መተዋወቅያ</u>" በማለት የጻፉትን መጽሐፍ ፣ ሁለተኛ እትም ፣ ክላሬንደን በተባሉ አሳታሚዎች እንግሊዝ አገር አክስፎርድ እ.ኤ.አ. በ1963 የታተመውን ፣ ከገጽ 243 እስከ 247 ይመልከቱ።

9 የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 989(1)

10 እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ግን አንድ ሰው በኑዛዜ የተደረገለትን ስጦታ አለመቀበሉ ያለኑዛዜ በሚያገኘው መብት የሚደርሰውን ውርስ ከመቀበል የማያግደው መሆኑ ነው። የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 989(2) እና(3) በተጨማሪ ይመልከቱ።

1. ቀላልና ምንም ገደብ የሌለበት የውርስ መቀበል፣
2. ከውርሱ በላይ ላለ ዕዳ ሀላፊነት የማያስከትል የውርስ መቀበል፣
3. ውርስን ለቅቄያለሁ ማለት፣

ቀላልና ገደብ የሌለው የውርስ አቀባበል የሚመረጠው ሟቹ በሕይወቱ እያለ ምንም ዓይነት ዕዳ የሌለበት መሆኑን ወራሹ በእርግጠኝነት በሚያውቅበት ጊዜ ብቻ ነው። ከወረሰኩት በላይ ላለ ዕዳ ተጠያቂ አልሆንም በሚል ገደብ የሚደረግ የውርስ አቀባበል የሚመረጠው ደግሞ

> ...የውርሱሀብት የሟቹን ዕዳ ለመክፈል በቂ ላይሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ ሲኖር ነው። ምርጫው በገደብ መደረጉ የባለገንዘቦቹ ጥያቄ ወደወራሹ የግል ሀብት እንዳይመጣ መከላከያ ይሆናቸዋል። በሌላም በኩል ዕዳ ተከፍሎ የሚተርፍ ነገር ቢኖር ያንን ለመውሰድም መብት ይሠጠዋል።[11]

ቀላልና ገደብ ባልተደረገበት የውርስ አቀባበል ምርጫ በኑዛዜም ይሁን ያለኑዛዜ የሟቹን ሀብት የራሱ ያደረገ ወራሽ ከተረከበው ሀብት በላይ ቢሆንም እንኳ ከውርሱላይ የሚጠየቀውን ግዴታዎችንም ግዴታ መወጣት ይኖርበታል።[12] ከውርሱ ያገኘውን ሀብት ግን ውርሱን እንደተቀበለ ያለምንም ውጣ ውረድ ወደያውኑየመጠየቅና የመረከብ መብት አለው። እንዲሁም በሆነ ጊዜ የውርስአቀባበሉ የውርሱንሀብት ልዩ አቋም ያስቀራል።[13] የውርስ ሀብት የሚባለው ነገር ቀርቶ ይህ ሀብት ከሌሎቹ የወራሹ የግል ንብረቶች ጋር ይቀላቀላል። ከውርሱ ገንዘብ የሚጠይቁ ባለመብቶች ወራሹ የወረሰውን ሀብት ዝርዝር እንዲያቀርብ መጠየቅ አያስፈልጋቸውም። በቀጥታ ጥያቄያቸውን በራሱ በወራሹ ላይ ለማንሳትና የግል ሀብቱንም አስከብረው መብታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ይችላሉ።

ከውርስ በላይ ላለ ዕዳ ተጠያቂ አልሆንም በሚል ገደብ የተደረገ አቀባበል ግን ለወራሹ ሁለት ጥቅሞችን ያስገኝለታል። በአንድ በኩል ለውርሱ ዕዳ የሚጠየቀው በወረሰው ሀብት ዋጋ ልክ ወይም ከውርሱ በተቀበለው ገንዘብ መጠን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የውርስ ማጣራቱ ሂደት ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የውርሱ ሀብትና የወራሹ የግል ንብረት ሳይደባለቁ ለየብቻቸው ይቆያሉ። የውርሱ ሀብት አካል የሆኑ ማናቸውም ንብረት ሁሉ ከውርሱ ላይ የገንዘብ መጠየቅ መብት ላላቸው ሰዎች የጋራ ዋስትናቸው ነው። በዚህ ጊዜ ወራሹ በወጉ የተረጋገጠ የውርሱን ሀብት የሚያመለክት ዝርዝር መግለጫ የማቅረብ ሀላፊነት አለበት።

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የ1952 ዓ.ም የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ሕግ የውርስ ማጣራቱ ሂደት ከመዘጋቱ በፊት ከውርስ በላይ ላለ ዕዳ ተጠያቂነት የለብኝም በማለት አንድ ወራሽ ውርሱን ለመቀበል ስለመቻሉ በግልጽ የሚለው ነገር የለም። ይህም ባይኖር በሕጋችን አንድ ወራሽ ከደረሰው የውርስ ሀብት

---

[11] ፕላንዮል፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 5 የተገለጸው መጽሐፍ፣ 3ኛ ሽልዩም፣ ክፍል 1፣ ገጽ 613፣ ትርጉም የራሴ፣

[12] ኮርፕስ ጁሪስ ሰኮንደም፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተገለጸው መጽሐፍ፣ አንቀጽ 1285፣ ገጽ 123፣

[13] የውርሱ ሀብት ተለይቶ የሚቀመጥ ነው ቢባልም በራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም አይደለም። ይህ ሀሳብ የሚገልጸው ውርሱ የሟቹን ሀብትና ዳ አጠቃልሎ የያዘ መሆኑን ብቻ ነው።

በላይ ውርሱ ለሚያመጣው ዕዳ ተጠያቂነት የለበትም። የዚህ ተጠያቂነት ውጤት ግን በሁለት የተለያዩ ደረጃዎች የተከፈለ ነው።

የውርስ ማጣራት ሂደቱ እዳር ከመድረሱ በፊት የውርሱ ሀብት ራሱን ችሎ እንደተለየ ንብረት ይቆጠራል። ይህ ሀብት ከውርሱ ገንዘብ የሚጠይቁ ወገኖችና የውርሱ ተጠቃሚዎች የጋራ መብት ተቀላቅሎ የሚገኝበት ያልተከፋፈለ ሀብት ነው።[14] በውርሱ ሀብት ላይ የሚያነሱትን ጥያቄ በተመለከተ ከሟቹ ላይ የሚጠይቁት መብት ያላቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ከወራሾቹ በግል መብት ከሚጠይቁ ባለገንዘቦች የተሻለ መብት አላቸው።[15] ወራሾች የውርሱን ሀብት ለመከፋፈል የሚያቀርቡት ጥያቄ ተግባራዊ የሚሆነው ሕጋዊ መብት አለን ብለው የቀረቡ የውርሱ ገንዘብ ጠያቂዎች ፥ ከውርሱ ሀብት የቀለብ ጥያቄ የማቅረብ መብት ያላቸው ወገኖች፥ እንደዚሁም የልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚዎች ድርሻ በሕጉ በተቀመጠው የአከፋፈል ቅደም ተከተል መሠረት ከተከፈለ በኋላ ብቻ ነው።[16] በዚህ የማጣራት ሂደት ውስጥ የውርሱ ሀብት ለቀረቡት ባለመብቶች ከተከፈለና የተረፈ ነገር ከሌለ አዲስ መጥ የውርስ ባለገንዘቦች በወራሾቹ ላይ በግል የሚያቀርቡት የመብት ጥያቄ አይኖርም። ወራሾቹ ራሳቸው ከዕዳ ተርፎ የተረከቡት የውርስ ሀብት የለምና።

በሌላ በኩል ትክክለኛና የበሰሉ የውርስ ዕዳዎች ከተከፈሉ በኋላ የተረፈ ነገር ካለ ይህን ሀብት ወራሾቹ እንደየድርሻቸው ይከፋፈላሉ። ይህ የሚቀበሉት የውርስ ንብረትም ከውርሱ ውጭ ካላቸው የግል ሀብት ጋር ይቀላቀላል።[17] ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚቀርቡት የውርሱ ባለገንዘቦች ከወራሾቹ በግል ዕዳ ከሚጠይቁ ባለገንዘቦች የተሻለ መብት በውርሱ ሀብት ላይ የላቸውም። እንዲያውም ያነሰ መብት ነው ያላቸው። ምክንያቱም ከውርሱ ሀብት ዕዳ የሚጠይቁት ባለገንዘቦች ወራሹን የሚጠይቁት በወረሰው ገንዘብ መጠን ብቻ ሲሆን በግል ችሎታው ወራሹን ዕዳ እንዲከፍል የሚያስገድዱት ባለገንዘቦች ግን የወረሰውንም ሀብት ሆነ ከውርሱ ውጭ ያለውን ሀብቱን በማስከበር ዕዳውን እንዲከፍል ሊያስገድዱት ይችላሉና ነው።[18]

ከዚህ በመነሳት ቀጥሎ ያሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ በኋላ ከውርስ በላይ ላለ ዕዳ አላፊነትን የማያስከትል የውርስ አቀባበል ደንብ በፍትሐ ብሔር ሕጋችንም አለ ብሎ መናገር ይቻላል።

1. ከውርሱ ሀብት ላይ ገንዘብ የሚጠይቁ ወገኖችና ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚዎች በቅድምያ ድርሻ ክፍያቸውን ይቀበላሉ።
2. ከዚህ ክፍያ የሚተርፍ የውርስ ሀብት ይኖራል።

---

14 የፍት.ብ.ሕ.ቁጥር 942፥ 943(1)፥

15 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 943(3) ፥

16 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1014 (የክፍያ ቅደም ተከተልን በተመለከተ)፥ ቁጥር 1052 (የውርስ መዘጋትን በተመለከተ)፥

17 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1053(1)፥

18 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1054፥ 1055፥

3. ይህ ተራፊ ሀብት ከወራሾቹ የግል ሀብት ጋር ይቀላቀላል አለበለዚያም በጋራ ንብረትነት ይያዛል።[19]
4. ከዚህ በኋላ አውራሹ ያልከፈለን ዕዳ አለን የሚሉ የውርስ ባለገንዘቦች ተያቄያቸውን በወራሾቹ ላይ ያቀርባሉ።

ሦስተኛው የወራሾች የምርጫ መብት ደግሞ ውርሱንለትቁያለሁ ወይም አልቀበልም ማለት ነው። ይህኛው መብት ወራሹ የተጠራበትን ውርስ አልፈልግም በማለት መብቱን በገዛ ፈቃዱ የሚለቅበት ነው። ወራሹ ውርሱንለትቁያለሁ በማለት ዕዳው ከሀብቱ መብለጡ ግልጽ በሆነ ውርስ ላይ ያለውን ተጠያቂነት በቀላሉ ማስቀረት ይችላል።[20] ውርስን አልቀበልም ማለት ጠቀሜታ የሚያስከትልበት ሌላው አጋጣሚ አውራሹ በሕይወት ዘመኑ በቂ የሆነ ልግስና ለወራሹ የሠጠው እንደሆነና ይህ ልግስና በአመላለስ ደንብ መሠረት ወደውርሱሀብት ሊደባለቅ በሚችልበት ጊዜ ነው።[21]

በዚህ ደንብ መሠረት " ውርሱን የሚቀበለው የሟቹ ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ... ተቀብሎት የነበረውን ዋጋውን ከውርሱ ውስጥ ማስገባት አለበት።"[22] በመሆኑም አንድ ወራሽ አንድ ጊዜ ውርሱን ለትቁያለሁ ካለ ለየትኛውም ጉዳይ ቢሆን የውርሱ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ስለሚቆጠር አስቀድሞ የወሰደውን ልግስና የመመለስ ግዴታ አይኖርበትም ማለት ነው።

## III

አልፎ አልፎ ደግሞ ውርስን የመቀበልም ሆነ የመልቀቅ ውሳኔ ለመስጠት አዳጋች የሆኑ አጋጣሚዎች የሚከሰቱበት ሁኔታም አለ። ቀጥሎ ያለውን ምሳሌ እስቲ እንመልከት።

"ሀ" በኑዛዜው ውስጥ ንብረትነቱ የ"ለ" የሆነውን አንድ ነገር "መ" ለተባለው ሌላ ሰው ይሠጣል። በዚያው ኑዛዜ "ሀ" ሌላ ንብረት ለ"ለ" ይሠጠዋል። "ለ" ለእርሱ የተደረገውን የኑዛዜ ስጦታ ከተቀበለ በኋላ የግል ንብረቱ የሆነው ነገር ለ"መ" የተሠጠበትን የኑዛዜ አንቀጽ መቃወም ይቻለዋልን? ውርሱንለትቁያለሁ የሚል ከሆነ በእርግጥም ተናዛዡ የሌላ ሰው ንብረት በሆነ ሀብት ላይ የማይቻል ኑዛዜ ስላደረገ ይህን

---

[19] ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1053(2)፥

[20] በኢትዮጵያ ከውርስበላይ ላለ የሟቹ ዕዳ ተጠያቂ የሚያደርግ ደንብ ስለሌለ ይህ አነጋገር በእኛ ሕግ ተግባራዊ ጠቀሜታ የሌለው መሆኑን መገንዘብ ይገባል። አንድ ሰው ውርሱንቢቀበልም ባይቀበልም ከውርሱ የሚመጣበት ዕዳ በወረሰው ሀብት ልክ የተወሰነ ነው።

[21] ፕላንዮል፥ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 5 የተገለጸው መጽሐፍ፥ 3ኛ ሽልዩም፥ ክፍል 1፥ ገጽ 613፥ ትርጉም የራሴ፥

[22] የፍት.ብ.ሕ. 1065፥ 1067 ፥ 1068 ፥ 1073፥

የሚመለከተው የኑዛዜው አንቀጽ ፈራሽ ነው ማለት ይቻላል።[23] ዳሩ ግን "ለ" ኑዛዜውን ከተቃወመ በሁለንተናዊ መልኩ ስለሚሆን በዝያው ኑዛዜ ላይ ለእርሱ የተደረገውንም ስጦታ እንደለቀቀ ሊያስቆጥርበት ይችላል። ውርሰን በከፊል መቀበል ወይም መልቀቅ በሕግ ተከልክሏልና።[24] በሌላ በኩል "ለ" ውርሱን ከተቀበለና "ሀ" ያደረገለትን የኑዛዜ ስጦታ ከወሰደ ሕግ ኑዛዜውን ለመቃወምና ለማስፈረስ የሠጠውን መብት አልሠራበትም እሚል መደምደምያ ላይ ያደርሳል። እንዲህ በሆነም ጊዜ "መ" በኑዛዜ የተሠጠውን የ"ለ"ን ንብረት መጠየቅ ይችላል።

ተመሳሳይ ጉዳይ ለአንድ የእንግሊዝ ፍርድ ቤት ቀርቦ ክርክር ከተካሄደበት በኋላ ፍርድ ቤቱ ቀጥሎ ያለውን አመለካከት በፍርዱ ላይ አስፍሯል። በዚህ ዓይነት በሚደረግ ኑዛዜ "... ትክክለኛ ንብረቱ ለሌላ የተሠጠበት አንድ ሰው እርሱም በበኩሉ በኑዛዜው ሌላ ስጦታ ያገኘ ሲሆን፣ ይህ ሰው በኑዛዜ የተሠጠውን ጥቅም ለቆ ኑዛዜውን ይቃወም እንደሆን አልያም በተናዛዡ ፍላጎት ይስማማ እንደሆን መምረጥ ይኖርበታል።"[25]

ይህን ምርጫ ከማድረጉ በፊት ግን የዚህ ዓይነቱ ሰው በኑዛዜ ለሌላ ሰው የተሠጠውን የግል ሀብቱን ዋጋ እርሱ በኑዛዜው ካገኘው ሌላ ሀብት ዋጋ ጋር በማነጻጸር ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም በቅጡ መመዘን ይኖርበታል። ከዚህ ከፍርድ ቤቱ ሀሳብ ለየት ያለ አመለካከት ያላቸው ጸሐፍት ደግሞ የሚሉት አላቸው።

> ... በሁለቱ ስጦታዎች መሀል ያለው የዋጋ ልዩነት ከፍተኛ የሆነ እንደሆነ ይህን አመለካከት እሥራ ላይ ማዋሉ ሚዛናዊ ላይሆን ይችላል... የንብረቱ ባለቤት የራሱን ንብረትም ሆነ በኑዛዜ ያገኘውን ስጦታ የመያዝ መብት ሊሠጠው ይገባል። ነገር ግን ይህ ሰው ለሌላኛው የኑዛዜ ተጠቃሚ የስጦታውን ንብረት ዋጋ በጥሬ ገንዘብ መክፈል አለበት።[26]

ይህን ችግር ከኢትዮጵያ ሕግ አኳያ የሚመረምር ሰው ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ ሊያነሳ ይችላል። ውርሰን በከፊል መቀበል ወይም አለመቀበል አይቻልም የሚለውን ደንብ ሳያፋልስ "ለ" ኑዛዜውን ከመቃወምና የራሱንም ስጦታ ከመጠየቅ ይከለከላል? መልሱ አከራካሪ ቢመስልም አይከለከልም የሚለው ነው። "አንድ ተናዛዥ በኑዛዜ የሚያስተላልፈው ንብረትነቱ የእርሱ የሆነውን ነገር ብቻ ነው፣ በሌላው ነገር ላይ ይህን ማድረግ ግን አይቻለውም።"[27]

---

[23] ዝኒ ከማሁ ፣ ቁጥር 865(2) ፣ 878፣

[24] ዝኒ ከማሁ ፣ ቁጥር 989(1)፣

[25] ደብሊዩ ጄ ዊልያምስ ፣ "ኑዛዜን የሚመለከት ሕግና ተሟልተው የተዘጋጁ የኑዛዜ ቅጾች" በማለት ካዘጋጁትና እ.ኤ.አ. በ1967 በሎንዶን ከተማ በበተርዎርዝስ አሳታሚዎች ለ3ኛ ጊዜ ከታተመው መጽሐፍ የተወሰደ ፣ ገጽ 224 ፣ ትርጉም የራሴ ፣

[26] ዝኒ ከማሁ፣ ትርጉም የራሴ፣

[27] ከርፐስ ጁሪስ ሰኩንደም ፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተገለጸው መጽሐፍ 94ኛ ቮልዩም ፣ ገጽ 782፣ ትርጉም የራሴ ፣ ሰረዝ የተጨመረ ፣

የተጠቀሰው መሪ ደንብ የሚያመለክተን አንድ ተናዛዥ የኑዛዜ ስጦታ የሚያደርገው የሚሠጠው ንብረት የእርሱ የራሱ ሲሆን ብቻ ነው። ለማንም ሰው ግልፅ እንደሚሆነው አንድ ተናዛዥ በሌላው ሀብት ላይ የሚያደርገው ስጦታ አይረጋም። ተናዛዥ ኑዛዜውን ባደረገ ጊዜ በተናዘዘበት ሀብት ላይ መብት እንዳልነበረው የማያውቅ መሆኑም በዚህ አሠራር ላይ የሚያመጣው የተለየ ውጤት የለም። በፍትሐ ብሄሩ ሕግ ላይ አንድ ኑዛዜ "አፈጻጸሙ የማይቻል እንደሆነ... ፈራሽ ነው።"[28] ተብሎ የተመለከተው አነጋገርም የዚህ ሀሳብ ገላጭ ድንጋጌ ነው። የሚቻል ኑዛዜ አንዱ ገጽታ ደግሞ ንብረቱ ከተናዛዡ ወደሌላው ያለችግር መተላለፍ የመቻሉ ጉዳይ ነው።

ከዚህ በመነሳት የቀረበውን ጉዳይ ስንመለከተው "ለ" ይህን የሕጉን ደንብ በመጥቀስ በእርሱ ሀብት ላይ የተደረገውን የኑዛዜ ስጦታ ውጤት እንዳያገኝ መጠየቅ ይችላል። ዳሩ ግን የዚህ የኑዛዜው አንድ አንቀጽ "... መሻር በዚሁ ያሉትን ሌሎች ቃላት መሻር አያስከትልም።" የአንዱ ቃል መሻር የሌሎችንም ቃላት መሻር የሚያስከትለው "... በእርግጠኛ አኳኋን በተናዛዥ መንፈስ ውስጥ ፈራሽ በሚሆነው ቃል አፈጻጸምና በሌሎቹ ቃላት አፈጻጸም መካከል አስፈላጊ የሚያስተሳስር ነገር ያለ መሆኑ ..." ሲታወቅ ነው።[29]

"ለ" በዚህ ደንብ መሠረት የእርሱ ንብረት ለሌላ የተሠጠበት የኑዛዜ ክፍል እንዲሻር ካደረገ በኋላ "መ" የ "ሀ"ን ኑዛዜ መግብያ በማድረግ የ"ለ"ን ንብረት መጠየቅ አይችልም። በዚህ ረገድ የሚነሳው ቀጣይ ጥያቄ ደግሞ "ለ" ይህን አድርጎ የ"ሀ"ን ኑዛዜ መቃወሙ በኑዛዜው የተደረገለትን ስጦታ እንደለቀቀ ያስቆጥረዋልን? የሚለው ነው። መልሱ አያስቆጥረውም የሚለው ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ውርስን ለቅቄያለው የሚለው መግለጫ በጽሁፍ ለውርስ አጣሪው የሚሠጥ አለበለዝያም አራት ምስክሮች ባሉበት በይፋ የሚገለጽ ነው። እንደዚሁም ምርጫው ቁርጠኛ በሆነ ቃል መገለጽ ያለበት ነው።[30] "ለ" ኑዛዜውን የተቃወመው ተናዛዡ "ሀ" ለመናዘዝ ችሎታ በነበረው ንብረት ላይ አይደለም። ይህን አድርጎ "ለ" ኑዛዜውን በሚቃወምበት ጊዜ የራሱን መብት ከማስከበር ባሻገር ውርሱንለመቀበል ወይም ላለመቀበል ብሎ የወሰደው እርምጃ እንደሆነ ተደርጎ ሊገመት አይገባውም። በመሆኑም ምንም እንኳን "ለ" የእርሱ ንብረት ለሌላ ሰው የተሠጠበትን የኑዛዜውን ክፍል የተቃወመ ቢሆንም በሌላው የኑዛዜው ክፍል ለእርሱ የተደረገውን ስጦታ ከመጠየቅ አይከለከልም ብሎ መከራከሩ ከሕጉ አኳያ አግባብ ነው።

## IV

በውርስ ሀብት ላይ ባለገንዘቦች የሚያነሱትን የመብት ጥያቄ በምንመረምርበት ጊዜ መዘንጋት የሌለብን ሁለት ዓይነት ባለገንዘቦች ሊኖሩ የሚችሉ መሆናቸውን ነው፣ እነዚህም ሟቹ ትቶት በሄደው ዕዳ ምክንያት የሚመጡ የውርሱባለገንዘቦች እና ከወራሾች በግል ዕዳ የሚጠይቁ የወራሾች ባለገንዘቦች ናቸው።

---

[28] የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 865፣

[29] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 878፣

[30] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 979(1)፣ 988፣

የውርሱባለገንዘቦች የሆኑ ሰዎች በመጣራት ላይ ያለው የውርስሀብት "ለገንዘባቸው ዋስትና መያዣ" የሚሆናቸው ሲሆን በወራሾቹ የግል ሀብት ላይ ግን ምንም መብት የላቸውም።[31] በሌላ በኩል የወራሾች ባለገንዘቦች ውርሱ ተጣርቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ በውርሱ ሀብት ላይ የመብት ጥያቄ ማንሳት አይቻላቸውም።[32]

የውርሱ ባለገንዘቦች እንደሁኔታው በመያዣ መብት ገንዘባቸውን ያስከበሩ፣ ወይም በሕግ የከፍያ ቅድምያ ያላቸው፣ ወይም ተራ ባለገንዘቦች ሊሆኑ ይችላሉ። ተራ ባለገንዘቦች ዕዳቸውን ያረጋገጡበት ምንም ዓይነት መያዣ ወይም ልዩ መብት የሌላቸው ናቸው። የየትኞቹም ዓይነት ባለገንዘቦች ጥያቄ የሚመለሰው ከውርሱ ሀብት ላይ ነው። ሟቹ ትቶት ያለፈው የዕዳ ዓይነትም ይህ ሰው በሕይወቱ እያለ ያልተወጣውን የውል ግዴታ ብቻ የሚመለከት ሳይሆን፣

> ... ከውል ውጭ በሚመጣ የፍትሐ ብሄር አላፊነትና ከወንጀል በሚመጣ ተጠያቂነት የሚነሱ የዕዳ ጥያቄዎችንም ያካትታል። በመሆኑም በወንጀል ፍርድ በሟቹ ላይ የተጣለየገንዘብ መቀጫ ከወራሾቹ ሊጠየቅ ይችላል። የወንጀል ክስ ገላጊ ጠባይ ያለውና ወደሌላ የማይተላለፍ ነው የሚለው ደንብ ተፈጻሚ የሚሆነው ክሱ ከሞተ በኋላ መቀጠል የሌለበት መሆኑን ለማመልከት ነው።[33]

ዋናው ጉዳይ የሟቹ ነው የተባለው ዕዳ በሕግ የታወቀና ሊፈጸም የሚችል መሆኑ ነው። በተቃራኒው ግን "... ሟቹ በሕይወት እያለ ቢቀርብበት ኖሮ ዋጋ የማይኖራቸው ሕገወጥና ፈራሽ መባል የሚችሉ ጥያቄዎች በውርሱ ሀብት ላይ መቅረብ አይችሉም።"[34] ከአንድ ሟች ለወራሾች የሚተላለፍ ግዴታ በራሳቸው በወራሾቹ ብቸኛ ፈጻሚነት ተግባራዊ እንዲሆን ብዙውን ጊዜ ባለገንዘቦች መጠየቅ ስለማይችሉ፡[35] ያላቸው ምርጫ ከግዴታው አፈጻጸም የሚያገኙትን መብት የሚያካክስ የኪሣራ ጥያቄ ማቅረብ ነው።[36] ግዴታው የሟቹን ብቸኛ ችሎታና የውል ፈጻሚነት የማይጠይቅ ሲሆን ባለገንዘቦች ሌሎቹን የተለያዩ አማራጮች ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። የውርስ አጣሪው ሟቹ አደርጋለሁ ብሎ የገባውን ግዴታ እንዲያደርግ ወይም እንዲያስደርግ ለመጠየቅ ይችላሉ፣ ሟቹ አስረክባለሁ ብሎ ግዴታ የገባውን ዕቃ ከሌላ ሥፍራ ለመግዛት እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ፣ በቂ የሆነ ምክንያት ሲኖራቸው ውርስ አጣሪው ለውሉ አፈጻጸም ያቀረባቸውን ንብረቶች ወይም ገንዘብ አንቀበልም ለማለት ይችላሉ፣ እንደዚሁም ሟቹ በህይወት እያለ ግዴታውን በውሉ መሠረት በሙሉና በብቃት ከመወጣት ችላ ብሎ

---

[31] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 943(1)(2)፣

[32] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 943(3)፣

[33] ፕላንዮል፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 5 የተገለጸው መጽሐፍ፣ 3ኛ ቮልዩም፣ ክፍል 2፣ ገጽ 12፣ ትርጉም የራሴ

[34] ኮርፐስ ጁረስ ሰኩንዶም ፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 ፣ የተገለጸው መጽሐፍ ፣ 34ኛ ቮልዩም፣ በአንቀጽ 367 በውርስ መጣራትና ማከፋፈል ከተገለጸው የተወሰደ ፣ ትርጉም የራሴ፣

[35] የፍት. ብ.ሕ.ቁ. 1776፣

[36] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 1790፣

እንደሆነ አለበለዚያ ይኸው ተግባር በውርስ አጣሪው ተፈጽሞ እንደሆነ ለግዴታው መነሻ የሆነውን ውል ለመሠረዝ ይችላሉ።[37]

ባለንገዘቦች አንድ ጊዜ በውርሱ ሀብት ላይ ያላቸውን የመብት ጥያቄ ካረጋገጡ በኋላ የዚህ የተረጋገጠው መብት ገቢራዊ አፈጻጸም ደግሞ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት የሚከናወን ነው። የፍርድ ውሳኔው ጥሬ ገንዘብ እንዲከፍል የሚያዝ ሲሆን የውርሱ ሀብት አካል የሆነን አንድ ንብረት አስከብር በማስሸጥ ገንዘቡ እንዲከፈል ይደረጋል።[38] እርግጥ ውርስ አጣሪው ወይም ወራሾቹ ገንዘቡን ከከፈሉ ወይም በሌላ በማናቸውም አመች መንገድ ዕዳውን ከዘጉ ይህ ሥርዓት ገቢራዊ አይሆንም።[39] የፍርድ ውሳኔው አንድን ተለይቶ የሚታወቅ ተንቀሳቃሽ ንብረት ለማስረከብ የሚያዝ ሲሆን ይህንኑ ንብረት ከውርሱ ሀብት ነጥሎ በማውጣትና ለባለመብቱ በማስረከብ ተፈጻሚ ይሆናል።[40] የፍርድ ውሳኔው የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት ሲሆን ደግሞ ባለገንዘቡ ይህን ንብረት በይዞታ እንዲረከብ ይፈቀድለታል። አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜም ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ የማይሆነው ባለይዞታ በሕግ ኃይል እንዲያስረክብ ይገደዳል።[41]

የዕዳው መክፈያ ጊዜ ከመድረሱ በፊትም ቢሆን የውርስ አጣሪው ወይም ወራሾቹ የውርሱ ሀብት አካል የሆኑትን ንብረቶች እያባከኑ መሆናቸውን የውርሱ ባለገንዘቦች ማረጋገጥ ከቻሉ ያላቸውን የመብት ጥያቄ ለማስፈጸም የሚያስችል በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲሠጣቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።[42] የዚህ ዓይነቱ የዋስትና ማረጋገጫ ካልቀረበ ባለገንዘቦቹ የውርሱን ሀብት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያስከብሩ ይችላሉ።[43] በተመሳሳይ ሁኔታ የውርሱ ሀብት አካል የሆነ ንብረት የሚጠፋ ወይም የሚበላሽ መሆኑን ባለገንዘቦቹ በሚያሳዩበት ጊዜ ንብረቱ ከመጥፋት እንዲድንና እንዳይበላሽ የሚያደርግ ትእዛዝ እንዲሠጥላቸው ለፍርድ ቤት ሊያመለክቱ ይችላሉ።[44] በዚህ ረገድ የጋቹ ንብረት ታሽጎ እንዲቀመጥ ወይም የታሸገው ንብረት እንዲለቀቅ የመጠየቅ መብት አላቸው። በተጨማሪም የውርሱ ሀብት

---

37 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1777-79፥ 1784፥

38 የፍት.ብ.ሕ.ሥ.ሕ.ቁ.394 ፥ ነጋሪት ጋዜጣ በተለይ የወጣ፥ ድንጋጌ ቁጥር 52/1958 ዓ.ም፥

39 ዝኒ ከማሁ፥ ቁ. 395(1)፥ 396(1)፥

40 ዝኒ ከማሁ፥ ቁ. 399፥

41 ዝኒ ከማሁ ቁ. 402 ፥ እነዚህ ደንቦች ንብረት አስከብር በማስሸጥ ገንዘቡን ለባለመብቱ መስጠት፥ ንብረቱን ከባለይዞታው ወስዶ ለባለመብቱ መስጠት፥ እና የማይንቀሳቀሰውን ንብረት አስለቅቆ ለባለመብቱ ማስረከብ እየተባሉ በፈረንሣይ ሕግ የሚታወቁት ናቸው ፥ በዚህ ረገድ <u>አምስና ዋልተን</u> ፥ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 8 የተገለጸውን መጽሐፍ ገጽ 240፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁ.ጥር 1 ይመልከቱ።

42 የፍት.ብ.ሥ.ሥ.ቁ.151፥እንዲሁም የፍት ብ.ሕ.ቁ. 1988፥

43 የፍት.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.152፥

44 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 154፥ እንደዚሁም የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 1992፥

ንብረት ዝርዝር እንዲዘጋጅ ለመጠየቅ ፣ በውርስ አጣሪው ወይም በወራሾቹ የተዘጋጀውን የውርስ ሀብት ክፍፍል ሥርዓት ለመቃወምና የሀብቱ ክፍፍል በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም ለመጠየቅ ፣ ይችላሉ።[45] ይህን በተመለከተ የውርሱ ባለገንዘቦች ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት፣

> የበሰለ ዕዳ የሚጠይቁ መሆናቸውንና ንብረቶቹ ሊበላሹ፣ ሊባክኑ ወይም ዋጋቸው ሊቀንስ እንደሚችል ማሳየት ከቻሉ ተያቄያቸው ተቀባይነት ያገኛል። የዚህ አሠራር ጠቀሜታ የባለገንዘቦች ጥያቄ አግባብነት ያለው ውሳኔ እስኪ ድረስ ይባክናል የተባለው ንብረት በፍርድ ቤት ባለሥልጣን አስተማማኝ ጥበቃ ሥር እንዲሆን ማድረግ ነው።[46]

ልክ እንደሌሎቹ ባለገንዘቦች ሁሉ የውርስ ባገንዘቦች የሚኖሯቸው ሌሎች አማራጮች ደግሞ በወራሾች መብት የመሥራት መብትና ተንኮል ያለበትን የወራሾች ተግባር የመቃወም መብት ነው። ሁለቱም መንገዶች ውሎች ውጤት የሚኖራቸው በተዋዋዮች መሀል ነው የሚለው አጠቃላይ ደንብ ልዩ ሁኔታዎች ናቸው።[47]

በባለዕዳው መብቶች የመሥራት መብት የውርሱ ባለገንዘቦች ውርስ አጣሪው ወይም ወራሾቹ ራሳቸው ሊሠሩባቸውናሊጠቀሙባቸው በሚችሉ መብቶች እንዲገለገሉ የሚያደርግ አሠራር ነው።እርግጥ እነዚህ መብቶች ከኋቹ የግል ችሎታ ጋርየተያያዙ ከሆኑ የውርሱባለገንዘቦች መጠቀምያ አይሆኑም። ይህን መብት ባለገንዘቦቹ ለመጠየቅ የሚችሉት ውርስአጣሪው ወይም ወራሾቹ ለውርሱ ሊገባ የሚገባውን ገንዘብ ከመጠየቅ ወደኋላ በሚሉበት ጊዜ ነው።የውርሱባለገንዘቦች ውርስአጣሪው ወይም ወራሾቹ የውርሱንገንዘብ ከሌሎች ባለዕዳዎች እንዳይሰበስቡ ለመከላከልና ኋቹ በሕይወት ቢኖር ኖሮ ሊያነሳ የሚችለውን ጥያቄ እንዳያነሱ ለመከላከል አይችሉም። የውርስባለገንዘቦች በወራሾች መብት ለመጠቀም የሚችሉት ወራሾቹ ወይም ውርስ አጣሪው የእነርሱን መብት በሚጎዳ አኳኋን ለውርሱ የሚገባውን ገንዘብ ከሦስተኛ ወገን ሳይሰበስቡ በሚቀሩበት ጊዜ ነው። ይህን መብት የሚጠቀሙትም ፍርድ ቤት ሲፈቅድላቸው ነው። ለውርሱ ሀብት የሚገባው ዕዳም የበሰለ ዕዳ መሆን ይገባዋል።[48]

ተንኮል ያለበትን የወራሾች ተግባር የመቃወም መብት ተግባራዊ የሚሆነው ደግሞ ውርስአጣሪው ወይም ወራሾቹ የሚፈጽሙት ተግባር በቀጥታ የውርሱንባለገንዘቦች መብት የሚጻረር ሲሆን ነው።የውርሱ ማጣራት ሥራ ከመዘጋቱ በፊት እያንዳንዱ የውርስ ባለገንዘብ የውርሱንሀብት በተጭበረበረ መንገድ ለሌላ

---

[45] ይህን በተመለከተ አጭርና ግልጽ ለሆነ ማብራርያ ኡብሬና ራው የተባሉ ጸሐፍት፣ "የፈረንሣይ የፍትሐ ብሄር ሕግ" በሚል ርዕስ በቮልዩም 4 ፣ ስለ ኀዱታ የጻፉትንና በሉዊዝያና ግዛት የሕግ ተቋም ከፈረንሣይኛ ወደእንግሊዝኛ ተመልሶ እ.ኤ.አ. በ1965 ለስድስተኛ ጊዜ የታተመውን መጽሐፍ ገጽ 124 እስከ 125 ይመለከቷል።

[46] አምስና ዋልተን ፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 8 የተገለጸው መጽሐፍ ፣ ገጽ 240፣ ትርጉም የራሴ፣

[47] የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 1952(1)፣ እንደዚሁም እላይ በማስታወሻ ቁጥር 8 የተሠጠውን ማብራርያ ይመልከቱ።

[48] ዝኒ ከማሁ ፣ ቁጥር 1993 ፣ እንደዚሁም ስለዚሁ ጉዳይ በፕላንዮል እላይ በማስታወሻ ቁጥር 5 ፣ 2ኛ ቮልዩም ፣ ክፍል 1 ከገጽ 173 እስከ 174 የተጻፈውን ይመልከቱ፣

ለማስተላለፍ የሚደረገውን ሥራ ሁሉ ሊቃወም ይችላል።[49] የተጠራበትን ውርስ ለቅቄያለሁ ያለ ወራሽ የግል ባለገንዘቦችም ቢሆኑ የዚህን ወራሽ አልፈልግም ማለት የመቃወም መብት አላቸው። ይህን መቃወሚያ ከማንሳታቸው በፊት ግን የወራሹ ውርሱን ለቅቄያለሁ ማለት በእነርሱ የመብት ጥያቄ ላይ የሚያስከትለውን ጎጂ ውጤት ማረጋገጥ አለባቸው።[50] ይህ ደንብ ቅን ልቦና የጎደላቸው ውርስ አጣሪዎች ወይም ወራሾች በሚፈጽሙት ተግባር ሰለባ ሊሆኑ የሚችሉ የውርስ ባለገንዘቦችን መብት የሚጠብቅ ነው። ውርስ አጣሪው ወይም ወራሾቹ "...የባለገንዘቦቹ ጥያቄና የሚያቀርቡት ክስ የውርስ ድርሻቸውን የሚያሳንስ ከመሰላቸው ሀብቱን ለመሸሸግ ጥረት ሊያደርጉ ይችላሉ።..."[51] በዚህ ረገድ የተለያዩ ዘዴዎችን ተንኮል ያሰበው ሰው ሊጠቀም ይችላል።

> ንብረቱን በግዢ ወይም በስጦታ አገኘሁ በሚል ሦስተኛ ወገን ጋር መመሣጠር በመፍጠር በዘዴ ባለገንዘቡን መጉዳት ይችላል፣ በገሀድ የሚታዩትንና በቀላሉ ተይዘው ለፍርድ አፈጻጸም ሊከበሩ የሚችሉ ንብረቶችን በጥሬ ገንዘብና ሊሸሽጉ በሚችሉ ሌሎች የንብረት ዓይነቶች ለመተካት ይችላል፣ ለራሱ ምንም ጥቅም ባያገኝ እንኳ ከተንኮል አስተሳሰብ በመነሳት የውርሱን ሀብት ለጓደኞቹና ለዘመዶቹ በማከፋፈል ባለገንዘቡን ሊጎዳ ይችላል። ከዚህም ሌላ ማለቂያ የሌላቸው የሰዎች ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ሊታወቁና ሊረጋገጡ በማይቻሉ እጅግ በርካታ መንገዶች የባለገንዘቦችን መብት ለመጻረር የሚያስችሉ አጋጣሚዎች ማመቻቸታቸው የሚጠበቅ ነገር ነው።[52]

ከዚህ ጋር አብሮ ሊነሳ የሚገባው አንድ ዓይነተኛ ፍሬ ነገር የወራሾች ባለገንዘቦች የዚህን ዓይነት ተንኮል በተመለከተ ሊያነሱ የሚችሉት የመብት ጥያቄ ነው። ባለገንዘቦች በወራሾች ምትክና በእነርሱ ሥፍራ ሆነው ውርስን ለመቀበልና ለመልቀቅ አይቻላቸውም። መብቱ የወራሹና የወራሹም ብቻ በመሆኑ ውርሱን እንዲቀበል ሊያስገድዱትም አይችሉም። በመደበኛው አሠራር የእነዚህ ባለገንዘቦች ጥያቄ በባለዕዳው የግል ሀብት ላይ የተወሰነ ነው። የዚህን ዓይነት መብት ተግባራዊ የሚያደርጉት የባለዕዳውን ዕዳ ለመክፈል አለመቻል በማሳየት ብቻ ነው። ወራሹ የግል ገንዘብ ጠያቂዎቹን ዕዳ ለመሸፈን የሚያስችለው ንብረት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ ባለገንዘቦቹ ወራሹ ውርሱን አልቀበልም ያለው እኛን ለመጉዳት ነው የሚል መከራከሪያ ለማንሳት አይቻላቸውም።

ይህን አሳብ ከዚህ ሰፋ አድርገን መመልከትም እንችላለን። ወደፊት ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚጠበቀውን የውርስ ሀብት ምክንያት በማድረግ ውርስ ከለቀቀ ወራሽ ጋር ቀደም ሲል ውል ያደረጉ ባለገንዘቦች የወራሹን ዕዳ ለመክፈል አለመቻል ቢያስረዱም እንኳ የተንኮልን መከራከሪያ ሊያነሱ አይችሉም። ለምሳሌም ያህል "ገና በሕይወት ባለው ሰው ውርስ ላይ ..." የሚደረጉ ውሎች በሕግ ፊት ዋጋ

---

49 የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 1995፣

50 ዝኒ ከማሁ ፣ ቁጥር 993፣

51 ፐላንዮል ፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 5 የተገለጸው መጽሐፍ 2ኛ ቮልዩም ፣ ክፍል 1 ፣ ገጽ 178፣ ትርጉም የራሴ፣

52 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 178-79፣ ትርጉም የራሴ፣

እያወጡም።[53] ቀጥሎ ያለውን ሁኔታ እንመልከት። "ሀ" ብር 50,000 ለ "መ" ያበድረዋል። በውሉ እንደተመለከተው የብድሩ ገንዘብ የሚከፈለው በበረታ ሕመም አልጋ ላይ የዋለው "ሠ" የተባለው የ"መ" አባት እንደሞተና እባንክ ሂሳቡ ውስጥ ያለው ብር 500,000 ለወራሾች እንደተከፋፈለ ነው።እንደተጠበቀውም "ሠ" ኑዛዜ ሳያደርግ ይሞታል። ውርሱ ተከፍቶ "መ" ሲጠራ ከአባቱ የሚያገኘውን የውርስ መብት መልቀቅንና ድርሻው "ረ" እና "ሸ" በተባሉት በሌሎች ወንድሞቹ ቢወሰድ የማይቃወም መሆኑን ያረጋግጣል። በዚህ ጊዜ "ሀ"የተንኮል መከራከሪያን መጠቀም ያ በማድረግ የ"መ"ን የውርስመልቀቅ ምርጫ መቃወም ይችላልን? መልሱ አይችልም ነው።

የውርስ ባለገንዘቦች የመብት ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ የመብታቸው መበላለጥና አለመበላለጥም መታየት አለበት። የውርሱ ሀብት የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥያቄ የሚሸፍን ከሆነና ሁሉም በእኩል ደረጃ የሚገኙ ከሆነ ፥ እንደዚሁም ጥያቄያቸው የበሰለና የተረጋገጠ ከሆነ ፥ በዕዳ አከፋፈል ላይ የሚኖር ምንም ችግር የለም። ችግሩ የሚነሳው የውርሱሀብት የሁሉንም የውርስባለገንዘቦች ዕዳ ለመክፈል የማይችል ሲሆን ነው። ይህን ችግር ከሁለት አቅጣጫ እየመረመሩ ማጥናት ይቻላል።

የመጀመርያው አጋጣሚ ክፍያ የጠየቁት የውርስ ባለገንዘቦች በእኩል ደረጃ ሆነው የውርሱ ሀብት የእነርሱን ጥያቄ በሙሉ ለመመለስ በማይችልበት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ሀብቱ የሚከፋፈለው በእያንዳንዱ ባለገንዘብ ጥያቄ መጠን ዕዳው በመቶኛ እየተተነተነ ነው።[54]

ሌላው ደግሞ በመያዣ ማረጋገጫ የገንዘብ ጥያቄያቸውን ያስከበሩ ባለገንዘቦች ወይም በሕግ የቅድምያ መብት ያላቸው ባለገንዘቦች ሲኖሩ ነው። የመያዣ ማረጋገጫ ያላቸው ባለገንዘቦች የሚባሉት የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ከባለዕዳው የያዙት ባለገንዘቦች ናቸው። በመያዣ ከሆነም "... የመያዣ መብት የተሠጠው ገንዘብ ጠያቂ...ከንብረቱ ዋጋ ላይ የሚጠይቀው ገንዘብ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች በፊት ለእርሱ በቀዳሚነት እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት አለው።"[55] ያለባለገንዘቡ ፈቃድ ባለዕዳው ይህን ንብረት ቢሸጠው ባለገንዘቡ ንብረቱን ከአዲሱ ገዥ እጅ ሊያስከብረው ይችላል።[56] የቅድምያ መብት የሚያስገኝለት ተግባር እንደመሆኑ መጠን ጥያቄውንበዚህ ዓይነት ማረጋገጫ ያስከበረ ባለገንዘብ በመያዣ የተረጋገጠውን ገንዘቡን በተመለከተ ከንብረቱ ሽያጭ ከሌሎች ባለገንዘቦች አስቀድሞ ይከፈለዋል።[57] በዚሁ ዓይነት ጥያቄውን በሚንቀሳቀስ የመያዣ ውል ያስከበረ ባለገንዘብም ከንብረቱ

---

53 የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 1114፥ "በሕግ ተገልጸው ከተፈቀዱት ሁኔታዎች ውጭ ገና በህይወት ባለ ሰው ውርስ ላይ ባንድ በኩል የሚደረጉ ውሎችና ግዴታዎች ሁሉ ፈራሾች ናቸው።"

54 የፍት.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.403 ፥ በባለገንዘቦች መሀል የሚደረገውን ድርሻ በተመለከተ ፥ ሮበርት አላን ሴድለር፥ የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ፥ ብለው በእንግሊዝኛ የዳፉትንና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ እ.ኤ.አ. 1968 የታተመውን መጽሐፍ ከገጽ 283 285 ፥ ይመልከቱ፥

55 የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 3059(1)፥

56 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 3059(2)፥

57 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር3076፥

ሽያጭ ላይ በመያዣው የተረጋገጠው ገንዘቡ ከሌሎች ባለገንዘቦች አስቀድሞ ይከፈለዋል።[58] የመያዣ መብት ያላቸው ባለገንዘቦች ከዚህ በተጨማሪ መያዣው ገንዘባቸውን የማይሸፍን ከሆነ ተራ ባለገንዘቦች የሚኖሯቸው መብቶች ሁሉ ይኖሯቸዋል። የመያዣ መብቱ ከሚያስገኝላቸው መብት ሌላ እንደማንኛውም ተራ የውርስ ባለገንዘብ የውርሱ ሀብት አካል የሆነ ንብረት ተከብር እንዲሸጥና ገንዘባቸው እንዲከፈላቸው ለማመልከት ይችላሉ። ከዚህም ሌላ ጥያቄያቸውን ወደሌላ ንብረት ከማስተላለፋቸው በፊት በመያዣ በያዙት ሀብት ላይ እንዲያስፈጽሙ የግድ አይጠበቅባቸውም።

በሕግ ልዩ መብት ያላቸው ባለገንዘቦች ከሥራ ውል በሚመነጭ ግዴታ ክፍያ የሚጠይቁ ሠራተኞች እንደዚሁም ግብር የመሰብሰብ መብት ያላቸው የመንግሥት አካላት ሊሆኑ ይችላሉ። የእነዚህም ጥያቄ ከተራ ባለገንዘቦች ጥያቄ ቅድምያን ያገኛል።[59]

በውርስ ማጣራት ሂደት ውስጥ ያለውን የውርሱ ባለገንዘቦች መብት በምንመለከትበት ጊዜ ሌላው መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ የመክፈያ ጊዜው ያልደረሰና በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ጥያቄ ያላቸው የውርስ ባለገንዘቦች ዕጣ ፈንታ ነው። የዚህ ዓይነት ባለገንዘቦች በሕግ ያላቸው መብት የመክፈያው ጊዜ ሲደርስ ወይም ሁኔታው ሲፈጸም ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ለማድረግ የሚያስችል የማረጋገጫ ዋስትና እንዲሠጣቸው ውርስ አጣሪውን ወይም ወራሾቹን መጠየቅ ነው።[60]

## V

በውርስ ማጣራቱ ሂደት የቀረቡት የውርስ ባለገንዘቦች ድርሻ ከተከፈለና ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚዎችም ስጦታቸውን ከተቀበሉ በኋላ የውርስ ማጣራቱ ሂደት ይጠናቀቃል።[61] ከዚህ የተረፈ ንብረት ካለ እንደነገሩ ሁኔታ በወራሾች የጋራ ባለቤትነት ሥር በመቆየት የሁሉንም ወራሾች ያልተከፋፈለ መብት ያካተተ ሀብት ሆኖ ይቆያል፣ አለበለዚያም የእያንዳንዱ ወራሽ ድርሻ እየተለየ ይሠጠዋል። ሁለቱም ዓይነት የንብረት ርክክብ መንገዶች የውርሱን ሀብት የተለየ ተቋምነት እፍጻሜ ያደርሳሉ። ከዚህ በኋላ ራሱን ችሎ እንደተለየ ንብረት የሚቆጠር የውርስ ሀብት አይኖርም ማለት ነው። በጋራም ሆነ በግል ወራሾቹ የተቀበሉት ንብረት ከግል ሀብታቸው ጋር ይቀላቀላል።[62] ንብረቱን ሳይከፋፈሉ ወራሾቹ በጋራ

---

58 ዝኒ ከማሁ ፣ ቁጥር 2857 ፣ 2858(1)፣

59 የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985፣ ነጋሪት ጋዜጣ 52ኛ ዓመት ቁጥር 27 ፣ አንቀጽ 167፣ እንደዚሁም የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 197/1947፣ ነጋሪት ጋዜጣ 14ኛ ዓመት ቁጥር 9፣ አንቀጽ 2(ሀ)፣

60 የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 1021፣

61 ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 1052(1)፣

62 ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 1053(1)፣

ከተቀበሉት ይህ ንብረት ያልተከፋፈለ የውርስሀብት ተብሎ መቆጠሩ ቀርቶ ባለመብቶቹ በጋራ ባለቤትነት እንደያዙት ሀብት ይቆጠራል።[63] እያንዳንዱ ወራሽ ድርሻውን ለይቶ ከወሰደ ደግሞ በውርስ ማጣራቱ ሂደት በተለይ ተቀምጦ በነበረው የውርስሀብት ውስጥ የሚገኘው የእያንዳንዱ ወራሽ ያልተከፋፈለ መብት በውል ተለይቶ ወደተመለከተ ጥሬ ገንዘብ ወይም ንብረትነት ይመነዘራል ማለት ነው።

ከፍ ብለን እንደተመለከትነው በሕጋችን ውስጥ ከውርስ በላይ ያለ አሳሬነትን የማያስከትል የውርስ አቀባበል ደንብ ተግባራዊ የሚሆነው በዚህ አኳኋን የውርስ ማጣራቱ ሂደት ከተዘጋ በኋላ አዲስ የውርስ ባለገንዘቦች ቀርበው ከሟቹ የሚጠይቁት ገንዘብ እንዲከፈላቸው በሚያመለክቱበት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ከውርሱጥቅም ያገኘው ወራሽ ተጠያቂነት በወረሰው ንብረት ዋጋ ወይም በተቀበለውገንዘብ መጠን የተወሰነ መሆኑንም እይተናል። ይህም ከውርስማጣራት በኋላ የሚቀርቡ የውርሱባለገንዘቦች ከወራሾቹ ባለገንዘቦች የተሻለ መብት በዚህ ደረጃ የሌላቸው መሆኑን የሚያሳየን ነው።[64] የውርስ ማጣራቱ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ የውርሱንላዳ እንዲከፍል የተጠየቀው ወራሽ ደግሞ የወረሰውን ንብረት ልክ ወይም የገንዘቡንመጠን የሚያመለክት የውርስንብረት ዝርዝርመግለጫ ማቅረብ ይኖርበታል።ይህ ማረጋገጫ ትክክል አይደለም የሚሉ ባለገንዘቦችም አባባላቸውን ማስረዳት ይችላሉ። የውርሱ ንብረት ዝርዝር አልተዘጋጀ እንደሆነ አለበለዝያም ዝርዝር መግለጫው ሊቀርብ ያልቻለ እንደሆነ የውርሱ ጠያቂዎች ውርሱ ምን ምን ንብረት ያካተተ እንደነበር በማናቸውም ማስረጃ ለማስረዳት እንደሚችሉ ሕጉ ይደነግጋል።[65]

ወራሹ የተቀበለውን ውርስ መሸሸጉን የውርሱባለገንዘቦች ካሳዩ ቅን ልቦና እንደሌለው ይገመታል። በዚህ ጊዜ ባለገንዘቦቹ በግል የሚሠጡት የተሸሸገው ንብረት ዋጋ በዳኞች ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል። ወራሹ ግምቱን የሚቃወም ሲሆን ባለገንዘቦቹ አባባላቸውን መሀላ በማውረድ ማረጋገጥ ይችላሉ። ይህን ሲያደርጉ ባለገንዘቦቹ ቅን ልቦና ያላቸው መሆኑን ሕግ ይገምታል።[66] ከውርስ ማጣራቱ በኋላ ወራሹ ድርሻውንመቀበሉ ከተረጋገጠ የተቀበልኩት ንብረት ጠፍቷል ወይም ተበላሽቷል በማለት ብቻ ያለበትን አሳሬነት ማውረድም አይቻለውም።[67]

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ችግር የውርስማጣራቱ ሂደት ከተዘጋ በኋላ የሚቀርቡ የውርስ ገንዘብ ጠያቂዎች ውርሱንበተቀበሉና ድርሻቸውንም በወሰዱ በርካታ ወራሾች ላይ ሊያነሱ የሚችሉት ጥያቄ ነው። እነዚህ ባለገንዘቦች በወራሾቹ ላይ የአንድነትና የነጠላ ክስ የማቅረብ መብት አላቸውን? መልሱ እንደነገሩ ሁኔታ አዎንታዊም አሉታዊም ሊሆን ይችላል።

ከውርስማጣራቱ ሂደት በኋላ የተረፈው ሀብት ሳይከፋፈል በወራሾቹ በጋራ ንብረትነት የተያዘ ከሆነ ባለገንዘቦቹ ወራሾቹን በማይነጣጠል አሳሬነት ሊከሱ ይችላሉ። የወረሱትን ንብረት በጋራ የያዙ ወራሾች

---

[63] ዝኒ ከማሁ ፥ ቁጥር 1053(2) ፥ 1060(1) ከቁጥር 1257 እስከ 1277 ካሉት አናቅጽ ጋር ያገናዝቧል።

[64] ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1054፥

[65] ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1055፥

[66] ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1056፥

[67] ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1057፥

ከውርሱ ገንዘብ ጠያቂዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ የአንድነትና የነጠላ ተጠያቂዎች ናቸው። የሁሉም ተጠያቂነት ግን ከውርሱ ባገኙት ሀብት ልክ የተወሰነ ነው።የወራሹ የግል ባለገንዘቦች ንብረቱን ማስከበር እንደሚችሉ ሁሉ የውርሱገንዘብ ጠያቂዎችም በውርስተላልፎ ወራሾች በጋራ የያዙትን ንብረት ለማስከበር ተያቂ የማቅረብ መብት አላቸው። በዚህ ረገድ የአንድነት ወራሾች በማይነጣጠል አላፊነት አብረው ከተቆራኙ የአንድነት ባለዕዳዎች ጋር የተመሳሰለ ገጼታ አለባቸው።[68]

ከውርስ ማጣራቱ ሂደት በኋላ እያንዳንዱ ወራሽ ድርሻውን በግል ተቀብሎ ወስዶ ከሆነ ደግሞ የውርሱባለገንዘቦች በወራሾቹ ላይ የአንድነትና የነጠላ ክስ ለማቅረብ አይቻላቸውም። የውርሱባለገንዘቦች ያላቸውን ዕዳ እየከፋፈሉ እያንዳንዱን ወራሽ በድርሻው መክሰስ ይኖርባቸዋል። ይህ ማለት ግን የውርሱ ባለገንዘቦች ሁሉንም ወራሾች በማጣመር ክስ አይመሰርቱባቸውም ማለት አይደለም። የእያንዳንዱ ወራሽ የዕዳ ድርሻ ተለይቶ በወረሰው ሀብት መጠን እየተተነተነ እስከተከሰሰ ድረስ ባለገንዘቦች ተከሳሾችን ስለማጣመር በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ የተመለከቱትን ደንቦች ሊሠሩባቸው ይችላሉ።[69] ይህም ሆኖ ሁሉም ወራሾች በድርሻ በድርሻቸው ተከሰው ከተወሰነባቸው በኋላ ከሌሎቹ ዕዳ የመክፈል አቅም የሌላቸው ከሆነ ቀሪዎቹ ወራሾች ሁሉንም ዕዳ ለውርሱ ባለገንዘቦች እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። ዕዳ የመክፈል አቅም የሌለውን ወራሽ የዕዳ ድርሻ ሌሎቹ ወራሾች በወረሱት መጠን ተከፋፍለው ይከፍሉለታል።[70]

ወራሾች የውርሱንባለገንዘቦች ተያቂ በወረሱት ሀብት መጠን ይመልሳሉ የሚለው ደንብ ሁል ጊዜ የማይሠራበት ሁኔታም አለ። በተለይም የባለገንዘቦቹ መብት ሊከፋፈል የማይችል ከሆነ በሁሉም ወራሾች ላይ ክስ እንዲመሠርቱ አይጠበቅባቸውም።[71] በዚህ ረገድ የማይከፋፈል መብት ሲባል አንድን ንብረት የመከተልና ከያዘው ሰው ላይ ማስለቀቅን የሚመለከት ነው።የዚህ ዓይነት መብት ያለው የውርስባለገንዘብ የሚፈልገውን ንብረት የያዘውን ወራሽ ንብረቱን እንዲያስረክበው በሚጠይቅበት ጊዜ ወራሹ በድርሻየ ነጥለህ ክሰሰኝ ብሎ ሊሞግተው መብት የለውም። በዚህ አኳኋን ተከሶ ይዞታውንየለቀቀ ወይም ንብረት ያስረከበ ወራሽ የሚኖረው መብት ሌሎቹን ወራሾች በድርሻቸው ዕዳውን እንዲከፍሉ መጠየቅ ነው። ወራሾች እርስ በርሳቸው ባላቸው ግንኙነት ሻጭ ለገዥው የሚኖርበት የመድን መስጠት ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ ከድርሻው በላይ ዕዳ የከፈለው ወራሽ ሌሎቹ ወራሾች የበኩላቸውን የዕዳ መዋጮ እንዲከፍሉት የማስገደድ መብት አለው።[72]

---

68 ዝኒ ከማሁ ፥ ቁጥር 1060(2) ከቁጥር 1259 ፥ 1260 እና 1896 ጋር ያገናዝቧል።

69 የፍት.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 36(1) " አንድ የክስ ምክንያት ብዙ ከሳሾችን የሚመለከት ሲሆንና ተከሳሾችንም በሕብረት ወይም በግምባር ለመክሰስ የሚቻል ሲሆን እንዲሁም በአንድነትም ሆነ በተናጠል ቢከሰሱ የሚወሰነው የሕግ ጥያቄና የሥረ ነገር ጭብጥ አንድ ሊሆን የሚችል በሆነ ጊዜ ተከሳሾችን በአንድነት አጣምሮ ለመክሰስ ይቻላል።'

70 የፍት.ብ.ሕ.ቁ. 1111፥

71 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1110(1)፥

72 ዝኒ ከማሁ ፥ ቁጥር 1097(1) ፥ 1113 ከ ቁጥር 2281 እስከ 2283 ካሉት ጋር ያገናዝቧል።

እዚህ ላይ የሚነሳው ሌላው አነጋገሪ ጉዳይ ደግሞ በልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተቀባዮችና የውርስ ማጣራቱ ከተዘጋ በኋላ በሚቀርቡ የውርስ ገንዘብ ጠያቂዎች መሀል ያለው ግንኙነት ነው። በውርሱ ማጣራት ሂደት የልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚዎች መብት ከውርስ ባለገንዘቦችና ከቀለብ ጠያቂዎች መብት ቀጥሎ የሚታይና እንደውርሱ ዕዳ የሚቆጠር ነው።[73] ይህም ቢሆን የዚህ ዓይነት ልዩ ስጦታ የተደረገላቸው ተጠቃሚዎች የውርሱን ባለገንዘቦች የዕዳ ጥያቄ ለመክፈል የሚገደዱባቸው አጋጣሚዎች አልፎ አልፎ ይከሰታሉ። እነርሱም ቢሆኑ ግን የውርሱን ዕዳ ለመክፈል የሚገደዱት በወረሱት ሀብት ልክ ብቻ ነው። ከዝያ በላይ ተጠያቂነት የለባቸውም። ይህ ብቻም አይደለም። ሊከሰሱ የሚገባቸው ወራሾች የውርሱን ባለገንዘቦች ዕዳ ያልከፈሉ እንደሆነ ነው። በዚህ አኳኋን የተከሰሰው ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚ የውርሱ ባለገንዘቦች አስቀድመው ወራሾቹን ሳይከሱ የጠየቁት እንደሆነ ሄዳችሁ ከወራሾች ተከራከሩ ብሎ የመጊገት መብት እንዳለው ሕጉ ይናገራል። በዚህ ረገድ ልዩ የኑዛዜ ተጠቃሚው ልክ በግዴታዎች ሕግ ውስጥ እንዳለው እንደተራ ዋስ ይቆጠራል።[74] በመሆኑም ክስ እንደተመሠረተበት አንድ ዋስ ማንሳት የሚችለውን መከራከርያ ሁሉ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚውም ሊያነሳ ይችላል። ባለገንዘቦቹን ከወራሾቹ ጋር አስቀድማችሁ ተከራከሩ በማለት ከውርሱ ያገኙትን ሀብትም ሆነ ሌላ የግል ንብረታቸውን በመጠቆም በእሱ ላይ ያለውን አላፊነት ማስወረድ ይችላል።

የዚህን ዓይነት መከራከርያ ባያነሳ እንኳ የቀረበበትን ክስ ተቀብሎ የውርሱን ባለገንዘቦች ጥያቄ ከመለሰ በኋላ እራሱን በባለገንዘቦቹ ቦታ በመዳረግና በእነሱም መብት በመሥራት ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚው ወራሾቹ የከፈለውን ገንዘብ እንዲመልሱለት ለማስገደድ ይችላል። በዚህ ጊዜ እሱ ራሱ እንደወራሾቹ ባለገንዘብ ስለሚቆጠር የውርሱን ዕዳ የመክፈል የመጨረሻ አላፊነት ያለባቸውን ወራሾች ገንዘቡን ክፈሉኝ ብሎ የመጠየቅ መብት አለው። ይሁንና በዚህ መብት ላይ ሁለት ማዕቀቦች ያሉ መሆኑ ማንዛቤ ሊሠጠው ይገባል።

ሀ) በተለያዩ ምክንያቶች ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚው ወራሾቹ ከተረከቡት ሀብት ግምት የበለጠ ዕዳ ለውርሱ ባለገንዘቦች ከፍሎ ከሆነ ወራሾቹ ከተቀበሉት ሀብት የበለጠ ገንዘብ ለእርሱ ለመመለስ አይገደዱም፥

ለ) አንድ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚ ድርሻህን አዋጣ በማለት በሌላ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚ ላይ ጥያቄ ለማቅረብ አይችልም፥[75]

---

[73] ዝኒ ከማሁ፥ "የውርሱን ዕዳ ስለመክፈል" የሚለውን የሕጉን አንቀጽ አምስት፥ ምዕራፍ ሁለት፥ ክፍል አራት ርዕስና ልዩ የኑዛዜ ስጦታ የከፍያ ቅደም ተከተልን አስመልክቶ በቁጥር 1014(ሠ) የተሠጠውን ስፍራ አገናዝበው ይመልከቱ፥

[74] ዝኒ ከማሁ ፥ ቁጥር 1058 ፥ 1934 ፥ 1935፥

[75] ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1059፥

# IV

ውርሱከተዘጋ በኋላ የወራሾቹ የግል ገንዘብ ጠያቂዎች በውርሱሀብት ላይ ከውርሱገንዘብ ጠያቂዎች ያነሰ መብት የሌላቸው መሆኑን እይተናል።[76] የተወረሰው ሀብት በወራሾቹ በጋራ የተያዘ ከሆነ የአንዱ ወራሽ የግል ባለገንዘቦች መብታቸውን ለመጠየቅ ያስችላቸው ዘንድ የእነርሱ ባለዕዳ የሆነው ወራሽ ድርሻ እንዲለይላቸው መጠየቅ ይችላሉ።[77] ሀብቱ እንዲከፈል ጥያቄ ካቀረቡ በኋላ እነርሱ ሳያውቁ መብታቸውን በሚጎዳ አኳኋን በወራሾቹ መሀል የተደረገውን የሀብት ክፍፍልም የመቃወም መብት አላቸው።[78]

ከውርስ ማጣራቱ የተረፈው ንብረት ለወራሾች ከተከፋፈለ በኋላ ደግሞ የወራሾቹ የግል ባለገንዘቦች በዚህ ወራሽ ድርሻ ላይ ጥያቄ ለማቅረብ መብት ይኖራቸዋል። በዚህ ረገድ ያላቸው መብት ልክ በወራሹ የግል ንብረቶች ላይ የሚኖራቸውን ያህል ነው።

በመጨረሻ የሚነሳው ጥያቄ አንድ ወራሽ ውርሱን አልፈልግም በማለቱ ድርሻው በሌሎች ወራሾች ከተከፋፈለ በኋላ የሚመጡትን የዚህን ሰው ገንዘብ ጠያቂዎች ዕጣ ፋንታ የሚመለከተው ነው። እነዚህ ሰዎች ወራሹ ውርሱን አልፈልግም በማለት የሠጠውን ማረጋገጫ ለመቃወም በሕግ የተመለከተው የሁለት ዓመት ጊዜ ከማለፉ በፊት ከቀረቡ ባለዕዳቸው ሊያገኝ የነበረውን ገንዘብ ከሌሎቹ ወራሾች ላይ ለመጠየቅ ይችላሉን?[79] ባለገንዘቦቹ ውርሱን አልፈልግም ያለውን ሰው ዕዳ ለመክፈል አለመቻል ካሳዩ በእርግጥም የዚህ ወራሽ አሠራር የባለገንዘቦቹን መብት የሚጋፋ ነው፥ ታድያ ሌሎቹ ወራሾች የዚህን ባለዕዳ የውርስ ድርሻ መልሰው ዕዳው እንዲከፈል ለማድረግ ይገደዳሉ?

በመደቡ አንድ ወራሽ በሌላው ወራሽ ዕዳ የሚጠየቀው ባለገንዘቦቹ የወራሹ የግል ሳይሆኑ የውርሱ ባለገንዘቦች በሚሆኑበት ጊዜ ነው። ይህ ወራሽ ዕዳ መክፈል ካልቻለ ሌላው ወራሽ የውርሱን ዕዳ ይከፍልለታል። በዚህኛው አጋጣሚ ግን ባለገንዘቦቹ የውርሱ ሳይሆኑ ከባለዕዳው በግል ችሎታው ገንዘብ የሚጠይቁ ናቸው። በጥቅሉ ስናየው ሌሎቹ ወራሾች የእርሱን የግል ባለገንዘቦች ጥያቄ ለመመለስ አይገደዱም ለማለት እንችል ይሆናል። ይሁንና ሕጉን ጠለቅ ብለን ስንመረምረው ውጤቱ ሌላ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን። የውርሱም ሆነ የወራሾች ባለገንዘቦች ወራሾቹ የሚሠሩትን ተንኮል ጠቀስ ተግባር የመቃወም መብት እንዳላቸው አይተናል። ባለገንዘቡ በይርጋ እስካልታገደ ድረስ ወራሹ የእርሱን መብት ሊጋፋ በሚችል መንገድ ያደረገውን የውርስ መልቀቅ መግለጫ ለመቃወም ይችላል። በውጤቱም ባለገንዘቦቹ የእነሱን ጥያቄ ሳያልፉ የውርስ መልቀቁን ተግባር ቀሪ ማድረግ ይችላሉ። የውርስ ክፍፍሉ ሂደት መቀላጠፍ በእነሱ መብት ላይ ጎጅ የሆነ ውጤት ሊያስከትል አይገባውም። የዚህን ዓይነት ባለገንዘቦች መብት ለመጠበቅ ሲባል ፍርድ ቤት የባለዕዳውን ውርስ መልቀቅ ውድቅ አድርጎ ሌሎቹ ወራሾች የተቀበሉትን የዚህን ወራሽ የውርስ ድርሻ ለዕዳው ክፍያ የማያውልበትና የእነዚህን ወራሾች የዕዳ ድርሻም

---

76 ዝኒ ከማሁ ፥ ቁጥር 1054(2)፥

77 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 1081(1)፥ 1260(2)፥

78 ዝኒ ከማሁ ፥ ቁጥር 1109፥

79 ዝኒ ከማሁ፥ ቁጥር 993(1)።

በተቀበሉት ሀብት መጠን በመቶኛ እየተሰላ የባለገንዘቦችየውርስተያቄ እንዲመለስ የማያደርግበትምክንያት የለም።

ነገሩን ለማጠቃለልም በ1952ዓ.ም. በወጣውየኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ሕግ ውስጥ ያለው የወራሾች የምርጫ መብት ወራሾችና የኑዛዜ ስጦታ ተቀባዮች አልፎ አልፎ ተፃራሪ ሊሆኑ በሚችሉት የውርስ መቀበልና አለመቀበል መብቶቻቸው እንዴት ሊሠሩባቸውእንደሚችሉ የሚያመለክተን ነው። ይህም በብዙ የሌሎች የሕግ ሥርዓቶችም ያለ ነው። የውርስማጣራት ሂደት ከመዘጋቱ በፊትም ሆነ ከተዘጋ በኋላ ሁለቱም አማራጮች የየራሳቸው ሕጋዊ ውጤቶች አሏቸው። የአንድ ውርስ ተጠቃሚ የሆነ ሰው በእነዚህ መብቶቹ ከመሥራቱ በፊት ውርስ በመቀበሉ ወይም ውርሱን አልፈልግም በማለቱ ሳቢያ ሊያገኘው የሚችለውን ጥቅም ወይም ሊደርስበት የሚችለውን አላፊነት በቅጡ መመዘን ያሻዋል። ከባለገንዘቦች መብት አኳያ ጉዳዩን ስንመለከትም እነዚህ ወገኖች የሚኖራቸው የጥያቄ አቀራረብ መብት በአመዛኙ በወራሾቹና በኑዛዜ ተጠቃሚዎቹ የተወሰደውን ምርጫ ገባ ብሎ በመመርመር ላይ የተወሰነ ይሆናል።